# ★ ዴሞክራሲያ ★

****************************************************

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

****************************************************

ቅጽ 33 ቁጥር 2 የካቲት 2000 ዓ. ም.


## ምርጫና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ

የምርጫ ጉዳይ ሲነሳ ለሕዝባዊ መንግስት ምስረታ የሚደረግን ሂደት ብሎም የሂደቱን ዴሞክራሲያዊነት ነውና ልናወሳ የተነሳነው የትናንቶቹ "የሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም"ና "ዴሞክራሲ ያለገደብ" መፈክር አንጋቢዎችን ዳግም ልናስታውስ ግድ ይለናል - የካቲት ላይ ነንና። የካቲት በመጣ ቁጥር፥ በ1966ቱ ሕዝባዊ አብዮት ዋዜማና ማግስት ለእኩልነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ሲሉ ክቡሩን የሕይወት መስዋዕትነት በፀጋ ተቀብለው እንደሻማ ነደውና ቀልጠው ብርሐን የሆኑንን ሰማዕታት ወጣቶች የምንዘክርበት ታሪካዊ ወር ነው - ከትናንት በስቲያ ፆታ ዘርና ዕድሜ ሳይለያቸው በአንድነት ወጥተው ያገራችንን ዳር ድንበር ከወራሪ ጠላት በመፋለም በነፃነቷ ታፍራና ተከብራ የኖረች ኢትዮጵያን ያስረከቡንን አያት ቅድም-አያቶቻችንን በፍፁም ሳንዘነጋ።

አለመታደል ሆኖ የትናንቶቹ ጀግኖች አባትና እናቶቻችን እንዲሁም ወጣት ታጋይ እህትና ወንድሞቻችን ተጋድሎ በሚዘከርበት ባሁኑ ወቅት ደግሞ አገራችን በጎሳ ፖለቲካ በከበሩና በደመቁ፣ በሕዝብ እንግልትና ስቃይ በሚስቁ፣ ፍፁም አምባገነኖች እጅ ወድቃለች። እኒህ ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ላለፉት አስራ ሰባት ዓመታት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር በዋለ የይስሙላ ምርጫ እያጭበረበሩና በዴሞክራሲ ስም እየማሉና እየተገዘቱ በጉልበት እየገዙ ቀጥለዋል። ትዝታው አብሮን እስካሁን ያለውን የግንቦት 1997 ዓ. ም. ምርጫ የህዝቦች ድልና ተከትሎት የታየውን የአገዛዙን ተፈጥሯዊ አረመኔነት ሳንረሳና ለዚያ ምርጫ መሰናከልና መደናቀፍ ግዙፍ ምክንያት የሆኑት ተቋማዊ ችግሮች አፍጥጠው ባሉበት ታሪካዊ ሁኔታ ህወሓቶች ዛሬም ስለሌላ ምርጫ በማውራት ላይ ይገኛሉ።

ምርጫውም ለሚያዝያ 2000 ዓ. ም. የታቀደ ሲሆን የአካባቢና የማሟያ ተብሎ ተሰይሟል፣ “37 ተወዳዳሪ ፓርቲዎች የመወዳደሪያ ምልክቶቻቸውን አግኝተዋል” ተብሏል። ከ90 በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች (ለዚያውም ብዙዎቹ በህወሓት አምሳል የተፈጠሩ) አሉ ብሎ አገዛዙ በሚደነፋበት አገር - የዴሞክራሲ መለኪያው የፖለቲካ ፓርቲ ብዛት ይመስል- 37 ፓርቲዎች ብቻ ለውድድር “ማለፋቸው” አስገራሚ ነው። እስከ30 ሚሊዮን ያህል መራጮች፣ ማለትም ለመራጭነት ብቁ ከሆኑት ዜጎች ውስጥ 90 ከመቶው ለሚያዝያው ምርጫ እንደተመዘገቡም የአገዛዙ ምርጫ ቦርድ ጠቅሷል። ከነዚህም 49 ከመቶው ሴቶች እንደሆኑ ገልጿል።

የህወሓት ቀልዶች ማለቂያ ስለሌላቸዉ የራሱ የፓርቲው ተወዳዳሪ እጩዎች በህዝብ ፊት ቀርበው 99 ከመቶውን ሕዝቡ መርቆና አጨብጭቦ እጩነታቸውን እንዳፀደቀለትና በአዲስ አበባ ብቻ የእጩዎቹ ቁጥር እስከ 32000 እንደሚደርስ ተናግሯል:: በመቀጠልም ከነዚህ ውስጥ "60 በመቶ የሚሆኑት የፓርቲው አባሎች ሳይሆኑ የፓርቲውን ዓላማ የሚደግፉ ናቸው" ተብሏል:: እንደተለመደው አዳማቂ ፓርቲዎችም ተቀራራቢ አሃዝ ያለው እጩ ለየክልሎቹ ማቅረባቸውም ተነግሯል::

በሌላ በኩል "ህጋዊና የፓርላማ አባል" የሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለመወዳደር ቢመዘገቡም፣ ቀድሞም ጠንቅቀው የሚያውቁት አምባገነኑ ህወሓት ዳግም አላፈናፍን፣ አላስቆም አላስቀምጥ ብሏቸው ዳግም እሮሮ ማሰማት ከጀመሩ ሰንብተዋል:: ኦብኮ ከግንቦት 1997 ዓ. ም. ወዲህ ከ300 በላይ አባሎቹ መታሰራቸውን ሲገልፅ፣ ይባስ ብሎ በአንድ ቀበሌ ከ300 በላይ እጩዎች እንዳይቀርቡ አገዛዙ ማገዱ እንደወትሮው ሁሉ አሁንም እውነተኛ ፉክክር እንዳይኖር ያበጀው የተለመደ የማጭበርበር ስልት ነው የሚል ክስ በተደጋጋሚ እያቀረበ ነው:: በተጨማሪም የተቃዋሚ ደጋፊ ተብለው በተጠረጠሩ ዜጎች ላይ ተጨማሪ ግብር የተጣለ መሆኑንና የምርጫ ጣቢያዎች ተብለው የተመደቡትም ፖሊስ ጣቢያዎችንና የህወሓት ሹማምንት ቤቶችንም እንደሚያካትት በምሬት እየተገለፀ ነው::

ዛሬም እንደትናንቱ በቂ ምላሽ ያላገኘ መሰረታዊ ጥያቄ "ምርጫ ምንድን ነው?" "ምርጫ ወደ ዴሞክራሲያዊ ግብ የሚያደርስ መንገድ ነው ወይስ በራሱ አልፋና ኦሜጋ ሆኖ እንዲያው ለይስሙላ ጊዜ እየጠበቀ የሚከወን ድርጊት ነው?" የሚለው ነው:: ይህንን ጥያቄ ዘርዘርና ሰፋ አድርጎ መመልከቱ ጠቀሜታው የጎላ ነው::

ዘመናዊ ምርጫ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮጳ በስፋት የታየ ክስተት ነው:: ቢሆንም ሕብረተሰቡን በሞላ ያሳተፈ አልነበረም:: እያደር ግን ሴቶችና በቁጥር አናሳ የሆኑ ክፍሎች በትግል ደረጃ በደረጃ መብታቸውን ለማስከበር በቅተዋል:: በሚስጥር ወረቀት ድምፅ መስጠት የተጀመረው በታላቋ ብሪታንያ እ. አ. አ. በ1872 ነው:: እንደሚታወቀው በአሜሪካና በእንግሊዝ ምርጫን የሚያካሂድ ማዕከላዊ ተቋም (ለምሳሌ እንደ ምርጫ ቦርድ ዓይነት) የለም:: በአሜሪካ የፌዴራል ምርጫ ኮሚሽን የተቋቋመው እ. አ. አ. በ1974 ከወተር ጌት ቅሌት በኋላ ሲሆን፣ ሃላፊነቱ ምርጫን ለማካሄድ ሳይሆን ከምርጫ ጋር በተያያዘ ለምርጫ የሚሰበሰብ ገንዘብን ለመቆጣጠር ነው:: በበለፀጉ አገሮች ምርጫን የሚያካሂዱት ነፃ ተቋሞች ሳይሆኑ ያካባቢ የመንግስት አካሎች ናቸው:: የእነሱን ጉድለቶች እየታዘቡ ሊያጋልጡ የሚችሉ ማሕበረሰባዊ ተቋማት አንጻራዊ ነፃነት አግኝተውና ጠንክረውም ስለሚንቀሳቀሱ ከፓለቲካ ፓርቲዎችና ከንግድ ድርጅቶች ንክኪ ባያጡም በሚያጋልጣቸው መንገድ የመንግሥት አገልጋዮች አይሆኑም::

በበለፀጉ አገሮች ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ያበቃቸው ዋና ምክንያት ከካፒታሊዝም ማደግ ጋር ተያይዘው የተፈጠሩ የደለቡ መደቦችና የኢኮኖሚ ዋልታዎች እንዲሁም አንፃራዊ ነፃነት ያላቸው ሲቪክ ማኅበራት ናቸው:: ይህም በሂደት እየዳበረ በመምጣቱ ሃብታም አገሮች ዛሬ ምርጫን ለማካሄድ ነፃና ማዕከላዊ ተቋም አያስፈልጋቸውም:: ይህም ሆኖ በበለፀጉ አገሮች ከምርጫ ጋር በተያያዘ ችግር አይነሳም ማለት አይደለም:: እንዲያውም አልፎ አልፎ የሚፈጠሩትን ችግሮች እንደ ህወሓት ያሉ አገዛዞች ለአምባገነንነታቸው እንደ ማጠየቂያ ይጠቀሙበታል:: ሆኖም በበለፀጉ አገሮች የሚከሰተው ችግር አልፎ አልፎ ሲሆን፣ ችግሩን ለማስወገድ ይቻል ዘንድ አስቀድመው የሚመሰረቱ ተቋሞች ቁጥርም አነስተኛ አይደለም::

በኢትዮጵያ በአፄውና በደርጉ ዘመን ምርጫዎች መካሄዳቸው የሚታወስ ነው:: ሁለቱም መንግሰታት ዴሞክራሲያዊዎች ነን ሲሉና እንደዛሬው የህወሓት መንግስት ከኛም ወዲያ ላሳር ብለው እምብዛም ራሳቸውን አላሞካሹና ወደኋላ ተመልሶ ምርጫዎቻቸውን መገምገሙ ብዙም ፋይዳ የለውም:: የህወሓትን የትናንትና ወቅታዊ ተግባራት ግን በቀላሉ

መርምሮ ዴሞክራሲያዊ እንዳልሆነ ድምዳሜ ላይ መድረሱ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ምርጫ ቦርዱም ነፃ እንዳልሆነ ቀደምቶቹ ምርጫዎች ብቻ ሳይሆኑ የ1997ቱ ብቻ እንኳን በዋና ምስክርነት የሚያረጋግጠው ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የወሰዱዋቸውን ሁለት አበይት አቋሞች መልሰን ስንመርመር ለወደፊቱ ብዙ ጠቃሚ ልምዶች የሚያካፍሉን ይሆናሉ፡፡ በዚህ ረገድ በጥሞና መታየት ያለበት አንዱ ጉዳይ ፓርላማ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ፓርቲዎች ተቀፍድደው የተያዙበት አስከፊ ቅራኔ ነው፡፡ ባንድ በኩል ሕገ-መንግስቱን ተቀብለው በሰላማዊ መንገድ በመታገል የኢትዮጵያን ሕዝብ ዴሞክራሲ ሊያጎናፅፉ እንደሚችሉ ደጋግመው ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግም ዴሞክራሲ በሚመጣበት መንገድ ላይ ግልፅነት እንደጎደላቸው ይታያል፡፡ የፓርላማ አባል የሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ይታሰራሉ፣ ይንገላታሉ፣ በአደባባይ ይረሸናሉ፣ ቢሮዎቻቸው ይታሸጋሉ፣ ይዘጋሉ፡፡ ፓርላማ ውስጥ በፖሊሲ ላይ የጎላ ለውጥ ለማምጣትም አልተቻላቸውም፡፡ ይባስ ብሎ ለሚያዚያ 2000 ዓ. ም. ምርጫ የህወሓት ሹማምንት ቤት ውስጥ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ድምፅ እንዲሰጡ ቀጠሮ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተቺዎቻቸው “ለህወሓት የውሸት ዴሞክራሲ ምስክርና አዳማቂ ከመሆን ያለፈ ሚና እየተጫወቱ አይደለም” የሚሏቸውን እንዴት ለማስተባበል እንደሚችሉም ለመገመት ይቸግራል፡፡ በጣም ዘገምተኛ በሆነ መንገድ እንኳ ጭል ጭል የሚል ዴሞክራሲ ስለማይታይ ከየት ወዴት እየሄዱ እንደሆነ በግልፅ ማሳየት አልቻሉም፡፡

በፓርላማ መቀመጫ የተሰጣቸውን ተቃዋሚዎች ይበልጥ ስንመረምር ደግሞ በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንገደዳለን፡፡ አንደኛው ወገን የግልን ጥቅም በአድርባይነት በማሳደድ አገራችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ጎዳና ስለ መጓዟ ደንታ የሌለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ አገሩን ከልብ የሚወድ ነገር ግን ፓርላማውን ጥሎ ቢወጣና በተከታታይ በምርጫ ካልተሳተፈ በህወሓት ሕገ መንግስት መሰረት “ህጋዊነቱን” ማጣቱ አስጨንቆት ተቀፍድዶ የተያዘ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሃቀኛ ተቃዋሚ ሃይሎች ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በጅምላ ማውገዝ ሳይሆን ሐቀኛውን ክፍል መለየትና ከሱም ጋር የትግል አንድነት ለመፍጠር መቻል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ካለፈ ስህተት ትምሕርት ይሆነን ዘንድ እዚህ ላይ አንድን አመለካከት ለመጥቀስ እንወዳለን፡፡ አንድ የተቃዋሚ ክፍል በፖለቲካ ቀኖና ተቀፍድዶ ተይዞ ተቃዋሚ ድርጅቶች በምርጫ 97 ተሳትፎ እንዳያደርጉ ቀስቅሶ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ምርጫው ግንቦት ላይ ሊካሄድ ይህ በቀኖናዊ ፖለቲካ የተቀፈደደ ክፍል የካቲት ላይ ባወጣው መግለጫው ላይ “መጭው የወያኔ ምርጫ (ግንቦት 1997 ማለቱ ነው) ነፃና ፍትሃዊ እንደማይሆንና የተቃዋሚ ድርጅቶችም በዚህ ምርጫ ለወያኔ ሽፋን ሰጭ መሆን እንደሌለባቸው ህዝቡ በሚገባ አስረግጦ ነግሮዋቸዋል፡፡…ይልቁንም ህብረታቸውን አጠንክረው ትግሉን በመምራት ለድል እንዲያበቁት በአፅንኦት አሳስቧቸዋል፡፡” ብሎ ጽፏል፡፡ ይሁን እንጂ በወቅቱ ይህ ቀኖናዊ አመለካከት ስለ ምን ዓይነት ትግል እንደሚያወራ በትክክል ግልፅ አልነበረም፡፡ በምርጫ 97 ዙሪያም የተደረገው ትግል በኢትዮጵያ ታሪክ አኩሪ እንጂ ይኸው ቀኖናዊ አመለካከት እንደሰበከው ለአገዛዙ ሽፋን መስጠትን ዓላማው አድርጎ አልተንቀሳቀሰም፡፡ ምርጫው ባይደረግ ኖሮ ወይም ቡድኑ እንደተመኘው ተቃዋሚዎቹ በምርጫው ባይሳተፉ ኖሮ ክስረት ከመከተሉም በላይ የህወሓት አውሬያዊ ገጽታ ባልተጋለጠም ነበር፡፡

ምርጫ 97 ቀደም ካሉት በህወሓት ቁጥጥር ስር ከተከናወኑ ምርጫዎች ለየት ሊል እንደሚችል ቀደም ብለው ምልክቶች ነበሩ፡፡ ህወሓትን በገንዘብ የሚረዱ ለጋሽ አገሮች ምርጫው ነፃ እንዲሆን ግፊት አድርገዋል፡፡ አገዛዙም አለቆቹን ለማስደሰትም ይሁን በራሱ ፕሮፓጋንዳ ራሱ መልሶ በመታለል ምርጫውን አሸንፋለሁ ብሎ አምኖ የገባበት ክስረት የመጨረሻ ውጤቱ የህዝቡን ትግል አንድ እርምጃ ከፍ አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ ተቃዋሚዎች የብዙሃን መገናኛዎችን ከመንግስት ጋር እኩልም ባይሆን እንዲጠቀሙ ማድረጉ፣ ቱባ ቱባ ሹሞቹ ከተቃዋሚ ወኪሎች ጋር እንዲከራከሩ ማድረጉ፣ የውጭ የምርጫ ታዛቢዎችን

ማስገባቱ፣ የተቃዋሚ ሰላማዊ ሰልፎችን መፍቀዱ፣ ከተቃዋሚ ፓርቲ ወኪሎች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር ፈቃደኛ መሆኑና መነጋገሩ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው:: ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርነው በወቅቱ ይህን ሁኔታ ለማየት ባለመቻል አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በቀኖናዊ መንገዱ በመንጎድ በታክቲክና ስትራቴጂ ረገድ ግዙፍ ስህተቶች እንዲሰሩና በምርጫ 97 የተቃዋሚዎች ተሳትፎ እንዳይኖር እንዲቀሰቅስ አድርጎታል::

ምርጫ 97 በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ከየካቲት 66 ቀጥሎ የተከሰተ ታላቅ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ነው:: ህወሓት ለ15 አመት ያህል ያገሪቱን ታሪክ እያራከሰ፣ የጎሳ መርዙን እየነሰነሰ፣ ጭቆናውን አስፋፍቶ የግፉ ፅዋ ሞልቶ መፍሰስ ሲጀምር፣ ከምርጫው አንድ ሳምንት በፊት እስከ ሶስት ሚሊዮን የሚደርስ የአዲስ አበባ ኗሪ ባደረገው ሰላማዊ ሰልፍ “በቃህ፣ በቃን፣ አንፈልግህም፣ ከስልጣን ውረድ” ብሎ ባንድ ድምፅ ለህወሓት የስራ መልቀቂያ የስንብት ደብዳቤ ሰጠ:: ጉዳዩ ሕዝባዊውን ተዓምር ላልጠበቀው ህወሓት ክፉኛ አስደንጋጭ ትዕይንት ነበር:: የባሰ እንደሚከተል ለመገመት እስከሚያቅተው ህወሓት በከፍተኛ ድንጋጤ የተዋጠበት ሁኔታም ተፈጠረ::

ለግንቦቱ ምርጫ ከ72 ሚሊዮን የወቅቱ ያገሪቱ ህዝብ፣ 26 ሚሊዮን ያህሉ ለምርጫው ተመዝግቦ ነበር:: ከነዚህም ውስጥ 48 ከመቶው ሴቶች ነበሩ:: በውጤቱም መራጩ ህዝብ ህወሓትን በማያሻማ ቋንቋ “ከስልጣን አንስተንሃል” ብሎ አሰናብቶታል:: የውጭ ታዛቢዎችና የውጭ ኗሪዎች በመሸጉባት በአዲስ አበባ ማጭበርበር ከቶውንም ስላልተቻለው፣ አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ በዜሮ እንደተሸነፈና “ተቃዋሚ” ሆኖ እንደሚታገል ለፈፈ:: ትንሽ ሳይቆይ ደግሞ የራሱን የምርጫ ህግጋት በመጣስ “በገጠሪቱ ኢትዮጵያና በጠቅላላው ባገሪቱ ለሌላ አምስት የአገዛዝ ዘመን አሸንፌያለሁ” ብሎ አይኑን በጨው ታጥቦ ቀረበ:: ህወሓት እንደተሸነፈ ከበቂ በላይ ያገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎች ማስረጃዎች ሲኖሩ ሽንፈቱን ለመሸፈንና ወደ “ድል” ለመለወጥ በማከታተል ያላደረገው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እርምጃ አልነበረም::

የአውሮጳ ታዛቢዎች (200 ያህሉ) እንደዘገቡት የድምፅ አቆጣጠሩ 10 ከመቶው ሙሉ በሙሉ የተጭበረበረ፣ 37 ከመቶው ደግሞ ያልተሟላ እንደነበር አመልክተዋል:: የካርተር ማዕከል እንኳ (50 ያህል ታዛቢዎች የላከው) አቆጣጠሩ ባንዳንድ ቦታ ችግር አሳይቷል በሚል ለመዘገብ ተገዷል:: ቅንጅት በ139 የምርጫ ክልሎች የተለያዩ ችግሮች እንደተፈጠሩና የህዝብ ድምፅ እንደተቀማ በማስረጃ አስደግፎ አቅርቧል:: በዚህም መሰረት በአማራ ክልል 53 ጣቢያዎች፣ በኦሮሚያ 33፣ በደቡብ 43፣ በአፋር 8፣ በሃረሪ 2 የምርጫ ክልሎች በድምሩ 139 ጣቢያዎች ላይ ህወሓት በግልፅ የህዝብ ድምፅ አጭበርብሯል:: ይህ ሁሉ ሆኖ አገዛዙ በችሮታው ለቅንጅት 108 ለህብረት ደግሞ 52 የፓርላማ መቀመጫዎች ሰጥቶ፣ ከ300 በላይ ለራሱ በመመደብ በጠራራ ፀሐይ በስርቆሽ ተሰማራ::

"የሌባ ዓይነደረቅ..." እንዲሉ ህወሓት በምርጫ ጣቢያዎች በግልፅ ያሸነፉትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች "በምርጫው ላይ ተፅዕኖ አድርገዋል፣ አጭበርብረዋል" በሚል በሃሰት እየከሰሰ በሂደቱ የተሸነፉትን ተወዳዳሪዎቹን መልሶ የማስመረጥ ግልፅ ማጭበርበር ከመፈፀሙም በላይ የምርጫ ሳጥኖችን እስከመገልበጥ የደረሰ ተራ ሌብነት ላይ መሰማራቱ ምርጫውን ለመቆጣጠርና በአሸናፊነት ብቻ ለማጠናቀቅ የነበረውን ዕቅዱን ገሃድ አውጥቶበታል:: በዚህም የምርጫውን ኢዴሞክራሲያዊና ነፃ አለመሆን በገዛ ራሱ ድርጊት ለኢትዮጵያ ሕዝብና በእንግድነት ለተገኙ የውጭ ሃገር ታዛቢዎች በማሳየቱ ለትዝብት በቅቷል::

ምርጫ 97 ካሳየን በጎ ምሳሌዎችና ተስፋዎች ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ዓቢይ ጉዳይ የወቅቱ የወጣቱ ሚና ነው:: የየካቲቱ ትውልድ የት ደረሰ? እየተባለ በሚጠይቅበት ወቅት ወጣቱ "እምቢ ለአገሬ፣ እምቢ ለመብቴ" ብሎ ለወገኑ አለኝታነቱን በማያወላዳ መልኩ አረጋግጧል፣ የወደፊቷ ኢትዮጵያ ተስፋነቱንም በተግባር አስመስክሯል:: የ97ቱ ምርጫ ያሳየን ሌላው ጉዳይ የጎሳ መርዝ የተረጨበት የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳ ተናክሶና ተለያይቶ

ይኖራል ብሎ ህወሓት ለዓመታት ቢመኝም በተቃራኒው አሮሞው፥ አማራው፥ ጉራጌው፥ ትግሬው፥ ወላይታው፥ አፋሩ ወዘተ በጠቅላላው ኢትዮጵያዊው ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዞ አገዛዙን “አይንህ ላፈር” “ከሁሉም በፊት ዴሞክራሲያዊ አንድነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያ ትበልጥብኛለች” ብሎ ፍርጥም ብሎ ግልፅ አቋሙን በይፋ ገልጧል፡፡ በዚህም ህወሓት በምርጫ 97 ወቅት ለዘመናት ያወናበደበትን የሃሰት ጭምብል እንዲያወልቅና የታለሉት ወዳጆቹ ሳይቀሩ ያፈሩበት ሁኔታና የአገዛዙ ምንነት የተጋለጠበት አጋጣሚም ተፈጥሯል፡፡ በዚህም ለኢትዮጵያውያን የዘመናት በአንድነት የመቆም ሕያውነት ዳግም ብርሃን ፈንጠቋል፡፡  ከዚህም በላይ ምርጫ 97 የኢትዮጵያ ህዝብ እድሉን ካገኘ በገንዘብ፣ በኃሳና በመሳሰሉ ጉዳዮች ሳይታለል በእርግጠኝነት ወኪሎቹን የመምረጥ ብቃትም እንዳለው ለወዳጅም ለጠላትም ያሳየበት ታሪካዊ አጋጣሚ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ህወሓት በግልፅ የሰረቀውን ድምፅ እንዲመልስ የኢትዮጵያ ሕዝብ  ባደረገው ሕዝባዊ ቁጣና ሰላማዊ ሰልፍ ላይ አግአዚ የተባለውን ነፍሰገዳይ ሰራዊቱን አሰማርቶ በይፋ ቁጥራቸው የታወቀ 193 ዜጎችን ረሽኗል፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በእስር ለረጅም ወራት መማቀቃቸውንና እስከ ዛሬም መድረሻቸው ያልታወቀ ዜጎች መኖራቸውን የምናስታውሰው በከፍተኛ ቁጭት ነው፡፡ የህወሓትን የግድያ ወንጀል እንዲመረምር የተቋቋመው ኮሚሽን አባላትም በማጣራት የደረሱበት የመጨረሻ ውጤት ማለትም የአገዛዙ ተጠያቂነትና ሙሉ ሃላፊነት እንዲለወጥ በህወሓት በኩል የደረሰባቸውን ከፍተኛ ግፊትና ማስፈራሪያ ባለመቀበል በርካታዎቹ የሚወዷትን አገራቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ትተው ወደ ውጭ አገር ለመሰደድ ተገደዋል፡፡ በምርጫ 97 ሳቢያም የህዝብ ድምፅ እንዳይሰረቅ መተከላዊ አቋም የወሰዱና ፓርላማውን ለመቀላቀል አሻፈረኝ ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች፥ እስከ አንድ ዓመት ተመንፈቅ ያህል በእስር ማቅቀዋል፡፡ አባላት ደጋፊዎቻቸውና ሌሎችም ንፁኃን ዜጎች የደረሰባቸው እንግልት ስቃይና መከራም አይዘነጋም፡፡

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በምርጫ 97 ዋዜማ የታዩት የዴሞክራሲ ጭላንጭል ውጤቶችም ሆኑ እየተኮረኮሙና እየተደበደቡም ቢሆን ያላሰለሰ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የነፃው ፕሬስ ጥረቶች ጨርሶ የሉም፡፡ የነፃው ፕሬስ በነፃነት መንቀሳቀስና ማበብ በተለይ በምርጫ ሂደት ወቅት ነፃና ያልተዛቡ መረጃዎች በመራጩ ሕዝብ ውስጥ ለማስረፅ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉና ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ ያለነፃ ፕሬስ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሊኖር አይችልም፡፡ በ1997ም ሆነ ከዚያ በፊት የተከናወኑት ምርጫዎች ሙሉ በሙሉ በህወሓት ቁጥጥር ስር ነበሩና ውጤታቸውም  ፀረ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን መልሶ በማስቀመጥ ነው የተጠናቀቁት፡፡ ዛሬም እንደገና የሕዝብ ድምፅ እንዲሰረቅ ምክንያት የሆኑት የተቋም ለውጦች ሳይደረጉ አገራዊ ምርጫን ድጋሚ ማሰብ፣ ምርጫ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አሸጋጋሪ ጎዳና መሆኑን መዘንጋት ይሆናል፡፡ ነፃ ምርጫን ለማከናወን ከሁሉም ፓርቲዎች ወኪሎች የተውጣጣ የምርጫ አስፈፃሚ አካል ወይም ከማንም ፓርቲ ያልወገኑ ታዋቂ ግለሰቦችን ያቀፈ ዝርዝራቸውም በፖለቲካ ፓርቲዎችና በመንግስት ስምምነት የሚፀድቅ የምርጫ ቦርድ ካልተዋቀረ በስተቀር አሁን ባለው መልኩ በድጋሚ የሚደረግ አገራዊ ምርጫ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ አይወስድም፡፡

የመማክርት ሸንጎ አባላት 12 የነበሩት በምርጫ 97 ወደ 200 ማደጋቸው እንደዋነኛ ማስረጃ እየተጠቀሰና፣ በዘገምተኛም ለውጥ ቢሆን ተቃዋሚው አንድ ቀን ስልጣን ሊይዝ ይችላል ወደሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ተቃዋሚው ወገን ከቶውንም ሊመራም አይገባውም፡፡ ምርጫ በነፃ ምርጫ ቦርድ ሳይመራና የነፃ ፍርድ ቤቶችና ሌሎች ዴሞክራሲያዊ ተቋሞች መኖር ሳይረጋገጥ ዘገምተኛ ለውጥን ማለም ብቻውን የአዙሪት መንገድ ብቻ ነው የሚሆነው፡፡

የአካባቢና የማሟያ የተባለውን የሚያዝያ 2000 ዓ. ም. ምርጫ አስመልክቶ በቅድሚያ የማሟያ ምርጫ የተባለው ውድቅ መሆን አለበት፡፡ በምርጫ 97 የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጣቸውን ህጋዊ ወኪሎች ወደ ጎን አሽቅንጥሮ ጥሎ አዳዲስና ለህወሓት ምቹ የሆኑትን ለማስመረጥ መዘጋጀቱ ህጋዊ ካለመሆኑም ሌላ የምርጫ 97 ድሎችን የሚቀለብስ በመሆኑ

ተቀባይነት የለውም፡፡ በምርጫ 97 ያሸነፉት ሕጋዊ ወኪሎች፣ የህወሓትን ፓርላማ ያልተቀላቀሉት የይስሙላ ሸንጎ በመሆኑ የመረጣቸውን ህዝብ ድምፅ ለማስከበር ቀጻሚ ትግል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለሆነም መራጩ ሕዝብ ለህወሓት ምላሹ “የማሚያ ምርጫ አይሻንም፡፡ ሚሚያ የሚሉ ምርጫ የፌዝ ነው፣ የጎደለውና መሚላት ያለበት ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ብቻ ነው” የሚል መሆን አለበት፡፡

የቀበሌና የወረዳ ምርጫዎችን አስመልክቶ በፖለቲካ ፓርቲዎች የሚመራ የተቀነባበረ ጥረት ይጠይቃል፡፡ መራጩም ህዝብ ከሙስናና ከአድርባይነት ነፃ የሆኑትን፣ ከገዥው ፓርቲ ጋር ያልተነካኩትንና ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማሸጋገር አጋር ሊሆኑ የሚችሉትን ለመምረጥ መቻል ይኖርበታል፡፡ ያካባቢ ሹማምንት (የቀበሌና የወረዳ) በህዝቡ የቀን ተቀን ኑሮ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ስላላቸው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች በትኩረት ሊመለከቱት ይገባል፡፡ ምርጫ ህዝብን ማደራጃና ማታገያ፣ ወዳጅና ጠላትን መለያና ማጋለጫ፣ እንዲሁም የወገንን ሰፈር ማጠናከሪያ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል ማጤን ያስፈልጋል፡፡

ዛሬ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ከፍተኛ ታሪካዊ ተልዕኮ ከፊታቸው ተደቅኗል፡፡ ህወሓት የሰላማዊ ትግል ህግጋትን የሚያከብር መንግስት ባለመሆኑ በሰላማዊ መንገድ የሚደረጉ ትግሎች ያላቸው ቦታ እጅጉን በጣም ጠባብ ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል ለሌሎች መብትን ለማስከበር ለሚረዱ የትግል መንገዶች ዓለም አቀፍና አካባቢያዊ ሁኔታዎችም እየከበዱ መጥተዋል፡፡ ሁለቱ ታላላቅ ተቃዋሚዎች (ህብረትና ቅንጅት) ተበድለውም ቢሆን ለአገር ሰላም በማሰብ ያቀረቡትን የጋራ የሽግግር መንግስት ሃሳብ ህወሓት ሲያጣጥለው ኃያላን ከሚባሉትም ሆነ ከሌሎች የሩቅና የቅርብ የአፍሪካ አህጉር አገሮች የጎላ ግፊት አልታየም፡፡ በቅርቡ የኬንያን የ2000 ምርጫ አስመልክቶ የተፈጠረውን ያህል እንኳን አፍሪካዊና ዓለም አቀፋዊ ግፊት በ97ቱ ምርጫ ወቅት አላየንም - የአውሮፓው ማኅበር ካሳየው ሙከራ በስተቀር፡፡ ይህም የችግራችን መፍቻ ቁልፍ ማን እጅ ውስጥ እንዳለ ትምሕርት ሰጥቶን አልፏል፡፡ በዚህ ላይ ዛሬ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጣዊ ሁኔታ አበረታች አይደለም፡፡ በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ሃቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እርስ በርስ መናቆራቸውን ትተውና ከሁሉም በፊት አገርና ህዝብን አስቀድመው አገር ቤት ያሉትና ውጭ ለመቆየት የተገደዱት የብሔር ድርጅቶችና ብሔር አቀፍ ድርጅቶች በጋራ እንደገና ጠንካራ የትግል አንድነትን ለመመስረት የሚያስችላቸው መድረክ ለመፍጠርና ለትግሉም መሪ ስትራቴጂ ለመንደፍ ብሔራዊ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ መጥራቱ ዛሬም የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ብለን እናምናለን፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!
ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያቸንፋል!!!